# Learning by Ear 2013

## "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" – "መዘዙን መቀበል"

EPISODE 16: የምስራች፣ መርዶ

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: ንጉሴ BRINGS ምህረት A LETTER**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

**SCENE 2: PUBLIC TELEPHONE**

- **ዳንኤል (M, 16)**
- **አቶ ካሳሁን: (M, 50)**
- **MAN (M, 40s)**

**SCENE 3: ምህረት HAS GOOD NEWS**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**

**SCENE 4: ትዕግስት IS RAPED BY ምኞቴ**

- **ምኞቴ (M, 35)**

- **ትዕግስት (F,15)**

**INTRO**

**1. NARRATOR:**

**ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ስለ አፍሪካውያን ታዳጊ ወጣቶች የሚተርከዉና ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ተከታታይ ትምህርታዊ ድራማ ነዉ። "መዘዙን መቀበል" የተሰኘዉን ሁለተኛው ዙር ድራማአስራ ስድስተኛውን ክፍል ማድመጥ ከመጀመራችን በፊት ባለፈዉ ምን ላይ እንዳቆምን መለስ ብለን እንቃኝ። ትዕግስት በዕድሜ ብዙ ከሚበልጣት የወንድ ጓደኛዋ ምኞቴ ጋር ኮብልላ ነበር።**

***KW BEGIN***

**2. EPISODE 13, LINES 9 – 10:**

ምኞቴ: ወደ አዲሱ ቤትሽ እንኳን ደህን መጣሽ ትዕግስት። ወይስ የምኞቴ ሚስት ማለት አለብኝ? ምን ይመስልሻል፣ አህ? (...)

ትዕግስት: ***(Laughs)*** በጣም ወድጄዋለሁ፣ አቶ ምኞቴ

***KW END***

**3. NARRATOR:**

ንጉሴ፣ ምህረት እና ዳንኤል በተለያዩ ምክንያቶች እስከ አሁንም ከትምህርት ቤት እንደታገዱ ናቸው፤ ንጉሴ በእጽ፣ ዳንኤል እና ምህረት ደግሞ ተኝተው ምህረት በማርገዟ ምክንያት ። ዳንኤል በእርስ በእርስ ጦርነት ምክንያት ሀገሩ ላቦሪያ ስላልተረጋጋች ወደ ሀገሩ ለመመለስም ሆነ  አባቱን በስልክ ለማግኘት አልቻለም። በዚህ መሀል የምህረት እናት ልጃቸው ትምህርት ቤት እንድትመለስ በጣም እየጣሩ ነበር። እንደውም ርዕሠ መምህሯን አነጋግረዋል።

***KW BEGIN***

**4. EPISODE 14, LINES 49 – 57:**

> **ወ/ሮ ሉሊት**: *(…)*ልጄ ለቤተሰቡ ትልቁ ተስፋ ናት። ከፍተኛ ትምህርት መማር የጀመረች ብቸኛዋ ሰውም ናት። እባክሽን አንድ እድል ስጪት፣ ርዕሰ መምህርት ሰብለ! (…)
>
> **ርዕሰ መምህርት ሰብለ** *(57)*: (…) የመጨረሻውን ውሳኔ የምሰጠው እኔ ሳልሆን የትምህርት ቤቱ የስነ- ስርዓት ኮሚቴ ነው።

***KW END***

**5. NARRATOR:**

ትዕግስት፣ ምህረት፣ ንጉሴ እና ዳንኤል በቀጣይ ምን ይግጥማቸዉ ይሆን? የእዚህ ድራማ ርዕስ “የምስራች፣ መርዶ” ይሰኛል። ምህረት ጎስቋላው መንደር ታንዲካ ውስጥ በሚገኘዉ ቤትዋ ሳህኖችን እያጠበች  ናት…

**SCENE 1: ንጉሴ BRINGS ምህረት A LETTER**

6. **ATMO: TANDIKA SLUMS, DAYTIME, INSIDE ምህረት HOUSE**
7. **SFX: UTENSILS BEING WASHED IN A BUCKET (NO RUNNING WATER)**
8. **ምህረት(HUMS AS SHE WASHES UTENSILS)**
9. **SFX: KNOCK ON DOOR**
10. **ምህረት:** ክፍት ነው!
11. **SFX: DOOR OPENS**
12. **ንጉሴ:** ሃይ እንዴት ነሽ ፣ ምህረት!
13. **SFX: STOPS WASHING**
14. **ምህረት:** **(Surprised)** ንጉሴ! እዚህ ምን ትሰራለህ?

***KW BEGIN***

15. **ንጉሴ:** ልግባ?
16. **ምህረት:** **(Embarrassed)** እኔ…እምም…ግባ! ቤቱ ግን ትንሽ ቆሸሾዋል፤ እያጸዳሁ ነበር…

***KW END***

17. **SFX: DOOR CLOSING**
18. **SFX: FOOTSTEPS ንጉሴ**

**19. ንጉሴ:** ርዕሰ መምህርት ሰብለ ካባረሩኝ እለት ጀምሮ አላየሁሽም።

እንዴት ነሽ?

**20. ምህረት:** **(shyly)** ደህና ነኝ። አንተስ?

**21. ንጉሴ:** እኔም ደህና ነኝ። መጠጣት እና ማጨስ አቁሜአለሁ። ታውቂያለሽ

ርዕሰ መምህርቷ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ እንደምችል

ነግረውኛል!

**22. ምህረት:** **(polite)** ያ ጥሩ ነው።.

**23. SILENCE**

**24. ንጉሴ:** እና እንዴት ነሽ አንችስ ,,,ታዉቂያለሽ ግን?

**25. ምህረት:** **(uncomfortable)** ምንም አይደለም,,,,, እና አሁን ምን ልታዘዝ

ንጉሴ?

**26. ንጉሴ:** አባቴ እና እኔ ርዕሰ መምህርት ሰብለን ልናናግር ሄደን ሳለ ይህንን

ደብዳቤ እንድሰጥሽ ልከዉኛል።

**27. ምህረት:** ቆይ አንዴ እጆቼን ላደራርቅ።

**28. SFX: HANDS DRIED ON CLOTHES**

**29. SFX: PAPER RUSTLE AS LETTER IS HANDED OVER**

**30. ምህረት:** አመሰግናለሁ።

***KW BEGIN***

**31. ንጉሴ:** (unsure) ታውቂያለሽ …አባቴ ለአዲሱ ዘበኛችን እዚህ አካባቢ ስለሚኖር እሱን ሊልከው ፈልጎ ነበር፣ ግን እኔ …እኔ ላይሽ ስለፈለግሁ…ማለቴ በቃ …ለመምጣት ወሰንኩ፡፡

**32. ምህረት:** (confused) እኔን ለማየት? ለምን?

***KW END***

**33. ንጉሴ:** ምህረት፣ ናፍቀሽኛል

**34. ምህረት:** ንጉሴ፣ እኔ…እያስቸገርከኝ ነው፤አላዉቅም፡፡

**35. ንጉሴ:** ይቅርታ፡፡ እንደዚያ ማለቴ አይደለም፡፡ ግን ለአንቺ ግልጽ መሆን እና የሚሰማኝን መንገር እንዳለብኝ ተሰምቶኝ ነዉ፡፡

**36. ምህረት:** (chuckles uncomfortably) ንጉሴ፣ በእውነት አሁን እንዲህ አይነቱን ዉይይታችንን አልወደድኩትም፡፡

**37. ንጉሴ:** (pause) እሺ…ለማንኛውም አሁን መሄድ አለብኝ፡፡ ደህና ሁኚ ምህረት፡፡

**38. SFX: FOOTSTEPS**

**39. ምህረት:** ደህና ሁን፣ ንጉሴ፡፡

**40. SFX: DOOR OPENS CLOSES**

**41. ምህረት:** **(to herself)** ምህረት፣ እንዴት አይነት ደደብ ነሽ! ዳንኤልን ሳይሆን እርሱን ነበር መምረጥ የነበረብሽ ። ነፍስ የሆነ ልጅ እኮ ነው! ስለ እኔ ደግሞ በጣም ነው የሚጨነቀው። **(sighs)** እስኪ ርዕሰ መምህርቷ ደብዳቤ ላይ ምን እንዳለ እንይ...

**42. SFX: OPENS LETTER**

**43. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 2: ዳንኤል AT PUBLIC TELEPHONE**

**44. ATMO: BUSY TOWN, PEOPLE & TRAFFIC**

**45. ዳንኤል:** **(to himself)** ወይ ጉድ! እኔ ዳንኤል ካሳሁን መቼም እዚህ አገር የህዝብ ስልክ እጠቀማለሁ ብዬ ፈጽሞ አስቤው አላውቀም ነበር! **(sighs)** ወይ ጉድ !

**46. SFX: PHONE IN PUBLIC PHONE BOOTH BEING PICKED UP**

**47. SFX: COINS BEING INSERTED**

**48. SFX: DIALS**

**49. SFX: RINGING TONE**

**50. SFX: PHONE BEING PICKED AT THE OTHER END**

**51. አቶ ካሳሁን** **(on phone, bad connection)** ሃሎ?

52. **ዳንኤል:** ሃሎ፣ ዳዲ! ዳዲ!

53. **አቶ ካሳሁን** ዳንኤል! እንዴት ነህ የእኔ ልጅ?

54. **ዳንኤል** (eager) እግዚአብሔር ይመስገን አባ የት ጠፋህ? ለወራት ላገኝህ ብሞክርም አልቻልኩም፡፡ እማዬ ደግሞ ሁል ጊዜ ለስራ እንደሄድክ ነው ስትነግረን የነበረው፡፡

55. **አቶ ካሳሁን** አናግረሀታል? ወላጆቿ ጋር ናት!ደህና ናት?

56. **ዳንኤል:** (confused) ይመስለኛል፡፡ያገባሀት ግን አንተ እኮ ነህ፡፡ ማወቅ ያለብህ ...

57. **አቶ ካሳሁን** (serious tone) ስማኝ ዳንኤል፣ ለእናትህ አትንገራት፤ እዚህ ሁኔታዎች ሁሉ ደህና አይደሉም፡፡ ያለሁት ተደብቄ ነው፡፡

58. **ዳንኤል** ተደብቄ? ለምን? ምን ተፈጠረ?

59. **አቶ ካሳሁን** ዜና አልተከታተልክም እንዴ? ሀገሪቷን ጦር ሠራዊቱ ተቆጣጥሮታል! የማዕድን ስራችንንበአዲሱ መንግስት ተነጥቀናል፡፡

60. **ዳንኤል:** (shocked) ምን? ሁሉንም ነገር አጥተናል?

61. **አቶ ካሳሁን** አዎን የእኔ ልጅ፡፡ (deep breath) በእዚያ ላይ ፖሊስ እያደነኝ ነው...

62. **ዳንኤል:** ምን? ለምን?

**63. አቶ ካሳሁን** **(uncomfortable)** **ስለ ገንዘብ ነክ ወንጀሎች… እና …እና የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ።**

**64. ዳንኤል** **(shocked)** **ዳዲ! እውነትህን ነው? ምን አደረግህ? እኔ እንዲህ ማድረግህን ላምን አልችልም…**

**65. አቶ ካሳሁን** **(lying, waves it off)** **በእርግጥ አላደረግሁም! ቢሆንም ለጊዜው ሁሉም ነገር እስኪረሳ ትንሽ መደበቅ አለብኝ** **(sighs)** **ለማንኛውም… ትምህርት እንዴት ነው?**

**66. ዳንኤል** **(hesitant)** **ዳድ፣ እኔ …እኔ…የሆነ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ።.**

***KW BEGIN***

**67. MAN:** **(shouts from behind)** **ሄይ፣ ስማ! ሰዉዬ  እዛ ፲ጋር ፍጠን እንጂ! ይህ የህዝብ ስልክ ነው እሺ። ረጅም ወሬ የምትፈልግ ከሆነ የራስህን ሞባይል ስልክ ግዛ!**

***KW END***

**68. ዳንኤል:** **ዳድ፣ ስማኝ። ከትምህርት ቤት ታግጃለሁ።**

**69. አቶ ካሳሁን** **ምን? ለምን?**

**70. ዳንኤል:** **የሆነች ልጅ አስረግዞኛል ብላ ከሰሰችኝ። እኔ ግን እውነቴን ነው አላደረግሁትም!**

**71. አቶ ካሳሁን** ዳንኤል ምን ችግር ገጠመህ? አንተን ውድ ትምህርት ቤት ለመላክ ያንን ሁሉ ገንዘብ ያፈሰስኩት እንድትማር እንጂ ሴቶችን እንድታስረግዝልኝ አልነበረም!

**72. ዳንኤል:** ዳዲ፣ እምልልሀለሁ እኔ አይደለሁም ያስረገዝኳት!

**73. አቶ ካሳሁን** **(angry)** አትዋሸኝ! **(pause)** አሁን የት ነው የምትኖረዉ ለመሆኑ? ምንስ ትበላለህ?

**74. ዳንኤል:** ጓደኛዬ በለጠ ክፍሉ ውስጥ አስገብቶኝ አብረን እናድራለን። ከተማሪዎች የምግብ ክበብ ምግብ ደብቆ እያመጣልኝ ነዉ የምበላዉ፡፡ አሁን ግን በቃኝ ሂድልን ብሎኛል፡፡

***KW BEGIN***

**75. አቶ ካሳሁን** ያቺ ርዕሰ  መምህርታችሁ ጭራቅ ነገር ናት እንዴ? ላቦሪያ ውስጥ ያለውን ሁኔታ እያወቀች እንዴት እንዲህ ታግድሀለች?

**76. ዳንኤል** አጎቴ አስረስ እዚህ እንደሚኖር ታውቃለች፡፡ ነገሮች እስኪ ረጋጉ ድረስ እርሱ ጋር እንድሄድ ነው የነገረችኝ፡፡ እኔ ግን አልወደውም!

**77. MAN:** **(from behind)** ሄይ፣ እዚያ ጋር ሰዉዬ፤ ፈጠን ፈጠን ብለህ አዉርተህ ዝጋ እንጂ!

***KW END***

78. አቶ ካሳሁን ዳንኤል፣ እኛ የካሳሁን ቤተሰቦች ኩሩዎች እንደሆንን አውቃለሁ፡፡ ቢሆንም ይህ በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ነው፡፡ እዚህ ያለውን ነገር ፊር እስካሲዘው ድረስ ሄደህ ኪሲምባ ውስጥ አጎትህ ጋር ተቀመጥ፡፡ ሰማኸኝ?

79. ዳንኤል ግን፣ ዳዲ …

80. አቶ ካሳሁን ተናገርኩ እኮዳንኤል፤ የነገርኩህን ታደርጋለህ! አሁን እኔ መሄድ አለብኝ፡፡ ደህና ሁን…

***KW BEGIN***

**81. SFX: CLICK AS CALL IS CUT AT THE OTHER END.**

82. ዳንኤል: ዳዲ…ቆይ! ኧረ ! ስማኝ! **(bangs the telephone receiver against phone booth in anger)**

**83. SFX: TELEPHONE RECEIVER HIT SEVERAL TIMES IN ANGER**

**84. MAN:** **(shouts)** ሄይ፣ ስማ! ስልኩን አትስበረው! እኛም ልንጠቀምበት እንፈልጋለን፡፡

***KW END***

85. ዳንኤል **(deep breath, to the man)** እሺ፣ እሺ…
**(to himself, sarcastically)** አመሰግናለሁ ዳዲ፡፡ ሌላ አማራጭ ያለኝ አይመስለኝም፡፡

**86. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 3: ምህረት HAS GOOD NEWS**

***KW BEGIN***

87. **ምህረት/ቅዱስ: (sing happily, song can be replaced with regional song)** “…ኮርኒያ ኮርናስሜ ናስሜ ናስሜ፤ ማንን ትፈልጋላችሁ ዛሬ በማለዳ !”2X

88. **SFX: CLAP CLAP**

89. **ቅዱስ:** “ደስተኛ የሆነ ይጨፍር! ” 2X

90. **SFX: STAMP STAMP**

91. **ምህረት:** “ደስተኛ የሆነ በጣም ይሳቅ” 2X ደስተኛ የሆነ በጣም ይዝለል 2X

92. **ምህረት/ቅዱስ:** “ ወንድማችን በርታ በርታ እንዳትረታ፤ እህታችን በርቺ በርቺ እንዳትረቺ

93. **SFX: STAMP STAMP**

***KW END***

94. **ምህረት/ቅዱስ: LAUGH**

95. **SFX: DOOR OPENS AND CLOSES, FOOTSTEPS ENTER**

96. **ወ/ሮ ሉሊት:**እናንተ ልጆች!,,,,ምህረት እና ቅዱስ። ምን ተገኘ?

***KW BEGIN***

97. ምህረት: (innocently) ምንም እማ። መደሰት ወንጀል ነው እንዴ? እየዘመርን ነው!

98. ወ/ሮ ሉሊት: (not convinced) እዚህ ቤት ውስጥ ሰው ፈገግ ሲል ካየሁ ዘመን አልፎኛል ብዬ ነው። ቅዱስ፣ ንገረኝ፣ እህትህ እንደዚህ የተደሰተችው ለምንድን ነው?

99. ቅዱስ/ምህረት: (laugh)

100. ወ/ሮ ሉሊት: እንዴ እስቲ ሁለታችሁም ንገሩኝ! አለበለዚያ ቅዱሴ ነገ ከረሜላ አይገዛልህም…

101. ምህረት: (laughing) ቅዱስ፣ እንዳትነግራት፣ እየዋሸች ነው። ያም ሆነ ይህ መግዛት አትችልም…

***KW END***

102. ቅዱስ: (cuts in) ምህረት ከርዕሰ መምህርት ሰብለ ደብዳቤ ደርሷታል። ወደ ትምህርት ቤት ልትመለስ ነው!

103. ወ/ሮ ሉሊት: (happily) ምን?

104. ምህረት: (happily) ቅዱስ፣ እውነት ነው! ምስጢር መጠበቅ አትችልም!

105. ቅዱስ: (laughs) ልጫወት መሄዴ ነው! (continues to sing the song as he leaves)

**106. SFX: FOOTSTEPS - ቅዱስ LEAVES**

**107. SFX: DOOR OPENS AND CLOSES**

108. **ወ/ሮ ሉሊት**: ምን ተገኘ?

109. **ምህረት**: ርዕሰ መምህርት ሰብለ ደብዳቤ ፅፈውልኝ ነው፡፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ በአንድ መስፈርትተመልሼ እንድገባ ፈቅደልኛል፡፡

110. **ወ/ሮ ሉሊት**: የእኔ ልጅ ይሄ ትልቅ የምስራች ነው!

111. **ምህረት**: ልክ ነው፣ አይደል እማ? ግን አንቺስ? እንደ ገና ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደሽ ነበር? ይህን ሁሉ ሰዓት እዚያ ምን ስታደርጊ ነው?

***KW BEGIN***

112. **ወ/ሮ ሉሊት**: **(sighs) (to herself)** ያ ፖሊስ ጣቢያ እንደዉ በጣም አስጠልቶኛል፡፡ በሄድኩ ቁጥር አሁንም ነገሩን እያዩት እንደሆነ ነዉ የሚነግሩኝኛል፡፡.

113. **ምህረት**: ምንድን ነው የሚያዩት? ከአባቴ ጋር የተያያዘ ነገር ነው?

114. **ወ/ሮ ሉሊት**: አይደለም፣ በእውነት የአባትሽ ጉዳይ አይደለም፡፡

***KW END*** **(sighs)** ምንአልባት አሁን እዉነቱን ልነገግርሽ የሚገባበት ጊዜው ነው፡፡ **(low voice)** ጉዳዩ ስለ እህትሽ ነው፡፡

115. **ምህረት**: እማ እኔ እኮ ግን እህት የለኝም!

**116. ወ/ሮ ሉሊት:** ከወራት በፊት መውለዴን ታስታውሻለሽ?

**117. ምህረት:** አዎ፡፡ ህጻኑ ሞቶ አይደል እንዴ የተወለደዉ!

**118. ወ/ሮ ሉሊት:** **(deep breath)** አይደለም፣ አልሞተችም፡፡ አሁንም በህይወት አለች ፤ እርሷን ለማስመለስ እየታገልኩ ነዉ! አባትሽ …አባትሽ ሸጧት ነበር፡፡

**119. ምህረት:** **(gasps)**

**120. MUSICAL INTERLUDE (tense music)**

**<u>SCENE 4: ትዕግስት IS RAPED BY ምኞቴ</u>**

**121. ATMO: NIGHT ATMO, INSIDE ምኞቴ HOUSE**

***KW BEGIN***

**122. SFX: PEN SCRIBBLING ON PAPER**

**123.** ምኞቴ: **(shouts from the bedroom)** እሽ የእኔ ቆንጆ ትዕግስት፣ ወደ አልጋው አትመጪም?

**124.** ትዕግስት**:** **(shouts, distractedly)** እሽ ምኞቴ የቤት ስራዬን ቶሎ ልጨርስና፣ እመጣለሁ!

**125.** ምኞቴ: ኧረ ባክሽ! እንዴ፤ ከእዚያ ወንበር ላይ እኮ አልነቃነቅ ካልሽ ይኸው ሁለት ሰዓትሽ፡፡.

**126. ትዕግስት፡** የእኔ ውድ፣ ትንሽ ብቻ ታገሰኝ፤ መጣች ሳትል አጠገብህ ከች ነው፡፡

**(to herself)** ወይ አምላኬ! ዝም ብሎ ሄዶ እንቅልፍን

አይለጥጥም እንዴ እዚህእኔን ከሚነዘንዘኝ?

**127. ምኞቴ:** ምን? አልሰማሁሽም፡፡

**128. ትዕግስት፡** **(shouts)** ጥቂት ደቂቃ ብቻ ስጠኝ አልኩህኮ፡፡

**129. ምኞቴ፡** ከሁለት ሰዓታት በፊትም ያልሽው ይሄንኑ ነው፡፡ ወደ አልጋው

የማትመጪ ከሆነ እራሴ መጥቼ እወስድሻለሁ፡፡.

**130. ትዕግስት፡** **(silent, keeps writing)**

**131. SFX: FOOTSTEPS - ምኞቴ APPROACHES**

**132. ምኞቴ፡** **(sweetly)** አንቺ የሆንሽ ቆንጆ ነገር፣ ዘጋሽኝ አይደል?

**133. SFX: PEN DROPPED**

**134. SFX: CLOTHES RUSTLING AS ምኞቴ GRABS ትዕግስት**

**135. ምኞቴ፡** **(acts out carrying someone)** ነይ እንጂ ምንድን ነው! ዝም

ብለሽ እንደዛ የምትዘጊኝ ከሆነ እራሴ መጥቼ አንከበክብሻለሁ፡፡

**136. ትዕግስት፡** **(laughing)** ተወኝ! ኧረ ተወኝ! ብያለሁ! እባክህ፣ ምኞቴ! የቤት

ስራዬን መጨረስ አለብኝ፡፡ ተወኝ ፡፡

**137. ምኞቴ፡** አይሆንም፡፡ አሁን የእንቅልፍ ሰዓት ነው፡፡

**138. ትዕግስት:** **(still laughing)** እሺ፣ እሺ …

***KW END***

**139. ምኞቴ:** ነይ፣ ትዕግስት፣ አንቺ ጣፋጭ ነገር! ሳሚኝ…

**140. SFX: THEY KISS**

**141. ምኞቴ:** **(seductively)** ነይ እንጂ፤ በቃ፣ እንተኛ…

**142. ትዕግስት:** ቆይ፣ ምኞቴ። መከላከያ መጠቀም አለብን። እንደ ጓደኛዬ ምህረት ማርገዝ አልፈልግም።

**143. ምኞቴ:** እንዴ፣ ትዕግስት። አንድ ላይ እየኖርን። ያ ማለት ባል እና ሚስት ነን። እነዚያ አስቀያሚ ነገሮችአያስፈልጉንም።

**144. ትዕግስት:** **(not amused)** ባክህን፣ ምኞቴ። ስለዚህ ጉዳይ ቀደም ብለን ተነጋግረንበታል። ቆይ እሺ፤ ስንት ጊዜ እንጨቃጨቅበት?

**145. ምኞቴ:** **(angry)** ሚስቴ መሆንሽን አስክትረጂ ድረስ ሁል ጊዜም። እና ሚስቴ እንደመሆንሽ፣ እኔን መታዘዝ አለብሽ። **(roughly)** ነይ እዚህ ጋር!

**146. SFX: COMMOTION AS ትዕግስት IS PUSHED AND PULLED**

**147. SFX: SOUND OF SOMEONE LYING / SITTING ON BED**

**148. ትዕግስት:** አው! እየጎዳኸኝ ነው! እጄን ልቀቀኝ!

**149. SFX: COMMOTION**

**150. ምኞቴ:** **(angry)** ነይ እዚህ ጋር ትዕግስት! ይሄ ልመና ነው የሰለቸኝ! ተንቀሳቀሽ!

**151. ትዕግስት:** አይሆንም! አሁን ከአንተ ጋር መተኛት አልፈልግም! ዞር በል!

**152. SFX: RUSTLING OF CLOTHES**

**153. ትዕግስት:** ተው! ተው፣ ምኞቴ፣ ባክህን! እየጎዳኸኝ ነው። አይሆንም! **(fade out)**

**154. <u>OUTRO - NARRATOR</u>**

እንደ ቀልድ የተጀመረው ነገር ለትዕግስት በድንገት ወደ አስፈሪ ቅዠትነት ተቀይሮባታል። አብራው በምትኖረው እና በምታምነው የወንድ ጓደኛዋ ተደፍራለች። እንዲያ ብታምነውም እሱ ግን አለመፍቀዷን በጭካኔ ሸሮታል። በሌላ በኩል ደግሞ ለጓደኛዋ ለምህረት ነገሮች በስተመጨረሻ መሻሻል ጀምረዋል። በቀጣይ ምን እንደሚከሰት ለማወቅ የሚቀጥለዉን ክፍል ድራማ ያድምጡ። የዛሬዉን ድራማ በድጋሚ ማድመጥ ከፈለጉ በድረ-ገጽ አድራሻችን **dw.de/lbe** ላይ ያገኙታል። ድራማዉን ከዛው ከድረ ገፁ ላይ ወደግል መዝገቦ ላይም መገልበጥ ይችላሉ። በፌስ ቡክ ገጻችን ላይ ሊከታተሉን እንደሚችሉ አይዘንጉ። ጤና ይስጥልን!